# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2016/02*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

## በግብርና ንግድ ሥራ ዘርፍ የመሪነት ሚና የተጫወቱ ሴቶች የተሸለሙበት ዓመታዊ ኮንፈረንስ ተካሄደ

*የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በግብርናው ንግድ ዘርፍ የንግድ ዕቅድ በመንደፍ አሸናፊ ለሆኑ የሴቶች የግብርና ንግድ ትስስር አባላትን ሽልማት ሰጠ*

**አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፤ ጥር 4 ቀን 2008 ዓ.ም.፡-** የሴቶች የግብርና ንግድ ሥራ አመራር ትስስር በአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (USAID) የግብርና ንግድ ሥራ ገበያ እና የእንስሳት ገበያ ልማት እንቅስቃሴዎች በኩል እ.ኤ.አ. የ2015 የንግድ ሥራ ዕቅድ ውድድር አሸናፊዎች ተለይተው የተሸለሙበትን ሁለተኛውን ዓመታዊ ኮንፈረንስ በዛሬው ዕለት አካሄደ፡፡ በዶሮ እርባታ ዘርፍ የተሰማራችው ራሔል ሙላት የከፍተኛው ሽልማት አሸናፊ ሆናለች፡፡ በተጨማሪም ኤጀንሲው በስድስት ወራት የሥራ አመራርና የንግድ ሥራ ሥልጠናና ክትትል ላይ ለተሳተፉ አዲስ የትስስሩ አባላት የምስክር ወረቀት የሰጠ ሲሆን፤ በአጠቃላይ ለ13 ሥራ ፈጣሪ ሴቶች 1.1 ሚሊዮን ዶላር አበርክቷል፡፡

በኢትዮጵያ በግብርናው መስክ ከተሰማሩ ዜጎች ወደ ግማሽ ያህሉ ሴቶች ናቸው፡፡ የፍጆታም ሆነ ለሽያጭ ለሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በማምረት ሂደት ላይ በመሳተፍ ረገድ ከፍተኛ ሚናም ይጫወታሉ፡፡ ይሁንና ምን አይነት እህሎች መቼ ለሽያጭ መቅረብ እንደሚኖርባቸው በቤተሰብ ደረጃ በሚተላለፈው ውሳኔ ላይ እምብዛም ሲሳተፉ አይስተዋልም፡፡ ለሥልጠና፣ለገበያ መረጃ፣እንዲሁም ለብድር አገልግሎት ያላቸው ውስን ተደራሽነት በግብርናው ንግድ የሚኖራቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የትስስሩ ዋና ዓላማ በግብርናው መስክ ከፍተኛ የሆነ  ግንባር ቀደም ሚና የመጫወት እምቅ አቅም ባላቸው ሴቶች ላይ በማተኮር በዘርፉ ያላቸውን ክህሎት አዳብረው በንግድ ዕቅድ አዘገጃጀት፣በአስተዳደር እና በገበያ ሥርዓት፣ እንዲሁም የዕድገትና የራስ መተማመን መንፈስን ሊያሰርጹ የሚችሉ የአመራር ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ሥልጠናዎችን መስጠት ነው፡፡ በተጨማሪም የትስስሩ አባላት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች የተደራጁ ሴቶች ላይ ያተኮረ የክትትል ፕሮግራም ላይ በመሳተፍ የልምድ ልውውጥ በሚያደረጉበትና ክህሎትና ዕውቀታቸውን በሚያዳብሩበት ሁኔታ ላይ ይሠራል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ምክትል ዳይሬክተር ራሞና ኤል ሃማዛዊ ባደረጉት ንግግር፡-“የአሜሪካ መንግሥት ሴቶችን በማብቃት ላይ ያተኮሩ እንቅስቃሴዎችን ይደግፋል፡፡ ሴቶች በንግድ ሥራ የመሪነቱን ሥፍራ የሚይዙበትና የንግድ ድርጅት ባለቤቶች የሚሆኑባቸው ዕድሎች ሰፊ ከመሆናቸውም በላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመስፋፋት ላይ ናቸው፡፡ የትስስሩ ቀጣይነት ያለው ስኬትም የሴቶች በግብርናው ዘርፍ የንግድ ሥራ ላይ መሰማራትን አስፈላጊነትና ሴቶች በኢትዮጵያ ዕድገት የሚኖራቸውን ሚና አጉልቶ የሚያሳይ ነው” ብለዋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የሴቶች የግብርና ንግድ ሥራ አመራር ትስስርን በግንቦት ወር 2007 ዓ.ም. የመሠረተው ሲሆን፤ ከአዲስ አበባ፣ከአማራ፣ከኦሮሚያ፣ከደቡብ እና ትግራይ ክልሎች የተውጣጡ 94 አባላት ነበሩት፡፡ በመጀመሪያው ዓመት 90 በመቶ የሚሆኑት የትስስሩ አባላት ፕሮግራሙን በስኬት አጠናቅቀዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የትስስሩ አባላት 1,200 ደርሰው፤ የኢትዮጵያ ሴቶችን ፍላጎት ለማሟላት በግብርና የንግድ ሥራ ዘርፍ ብቁ የሆኑ አርአያ ሴቶችን በማነጽ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህም የሴቶች የንግድ ድርጅቶችን የማቋቋምና በዘርፉ አርአያዎችን የማፍራቱ ሥራ ጊዜ የማይሰጥ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

***

*የግብርና ንግድ ሥራ ገበያ እና የእንስሳት ገበያ ልማት እንቅስቃሴዎች መጪውን ትውልድ መመገብ የተሰኘ የአሜሪካ መንግሥት መርሀ ግብር ወሳኝ እንቅስቃሴዎች ሲሆኑ፤ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ለኢትዮጵያ መንግሥት የግብርና ዕድገት የሚሰጠው ድጋፍ ማሳያ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ረሃብን ለማጥፋትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ 3.5 ቢሊዮን ዶላር በመመደብ በቁርጠኝነት የሚንቀሳቀሰው የአሜሪካ መንግሥት የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዋንኛ የማዕዘን ድንጋይ የሆነውን የግብርና ዘርፍ በማሳደግ ረገድ ግንባር ቀደሙን ድርሻ የሚያበረክት አጋር ነው፡፡*

*For more information, see https://www.usaid.gov/ethiopia*